ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ነሐሴ 1999 ዓ.ም.

# የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 10

# የመሬት ሥሪትና የአርሶ አደሩ ቴክናሎጂያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ

♦ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❋❋❋

♦ የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❋❋❋

♦ በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❋❋❋

♦ በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❋❋❋

♦ በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## 1. መግቢያ

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የግብርናው ዘርፍ በተለይም የአርሶ አደሩ ክፍለ ኢኮኖሚ ለገጠሩ ሕዝብ የኑሮ ዋስትናና ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ዋነኛ አውታር ነው:: አርሶ አደሩ ወደ ዘጠና በመቶ የሚደርሰውን የግብርና ምርት ሲያመርት እንዲሁም ጠቅላላ ለእርሻ ከሚውለው መሬት ወደ ዘጠና ከመቶ የሚደርሰውን ያርሳል:: ሆኖም ስልሳ አምስት ከመቶ የሚሆነው አርሶ አደር ከአንድ ሄክታር በታች መሬት ሲኖረው የአርባ ከመቶው አርሶ አደር የመሬት ይዞታ መጠን ግማሽና ከግማሽ ሄክታር በታች ነው:: በሌላ ወገን የአርሶ አደሩ ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነት ዝቅተኛ ነው:: ለምሳሌ የአርሶ አደሩ ሰብል እርሻ መሬት ሦስት እጁን የሚሸፍኑት ዋነኛ ሰብሎች ማለትም የብርዕና የአገዳ ሰብሎች (Cereals) የሚሰጡት አማካኝ ምርት በሄክታር 12 ኩንታል ነው:: ይህም ከአለም አማካይ ደረጃ ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ነው:: የግብርና ዘርፍ በተለይም የአርሶ አደሩ ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነት ማነስ ለገጠሩ ሕዝብ የምግብና የገቢ ዋስትና ማጣት ከሚጠቀሱት ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ነው::

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአንድ ቤተሰብ የነፍስ ወከፍ የመሬት መጠን እየቀነሰ፣ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እያደገ ባለበትና ከግብርና ውጪ የሆኑ የኑሮ መተዳደሪያ ምንጮች ውስን በሆነበት ሁኔታ ዋነኛው የግብርና ኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂ ከተወሰነ መሬት መጠን ከፍተኛ ምርት ወይም እሴት የሚያስገኘውን መንገድ (Intensification) መከተል ነው:: ይህም በሚከተሉት ሦስት አካሄዶች ተግባራዊ ሊሆን ይችላል::

➔ ሁሉንም የምርት ግብአቶች (የሰው ኃይል፣ መሬት፣ ማዳበሪያ ወዘተ.) መጠን በተመጣጠነ መልክ መጨመር፣

➔ ከፍተኛ የገበያ ዋጋ ያላቸው ምርቶች ተክቶ ማምረት፣

➔ የመሬት ምርታማነትን የሚጨምር የተሻሻለ ቴክሎኖጂ መጠቀም፣

### *ዘለቄታ ያለው ምርታማ ግብርና ሥርዓት*

የተለያዩ ጥናቶችና ፅሑፎች እንደሚጠቁሙት ዘለቄታ ያለው ምርታማ የግብርና ሥርዓት መገንባት ለአርሶ አደሩ የኑሮ ዋስትናና ለጤናማ የግብርና ኢኮኖሚ ልማት ቁልፍ ስልት ነው:: ዘለቄታ ያለዉ ምርታማ የግብርና ሥርዓት ለማጐልበት የተሻሻሉና ተገቢ የግብርና ቴክኖሎጂ መጠቀም ያሻል:: ለዚህም የመሬት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችና ተግባሮ ችን (ለምሳሌ የአፈርና የውኃ ጥበቃ) ምርታማነትን ከሚጨምሩ ግብአ ቶች፣ (ለምሳሌ የተሻሻሉ የሰብል ዝርያ ዎች፣ ማዳበሪያ) አጓዳኝቶ መጠቀም ይጠይቃል::

ዘለቄታ ያለው ምርታማ ግብርና ሥርዓት ለማጐልበት እላይ ከተጠቀሱት ቴክኖሎጂዎች በተጨማሪ ሌሎች የተያያዙ ነገሮች በማጐልበቱ ሂደት ላይ የራሳቸው ሚና ይኖራቸዋል:: ለምሳሌ የአርሶ አደሩ የትምህርትና የሙያ ደረጃ፣ የማህበረሰቡ ባህላዊ እሴት፣ የምርቶችና ግብአቶች ዋጋ፣ የመሬት ይዞታ ስሪት፣ የአካባቢው ሥነ-ምህዳርና የአየር ንብረት ዘለቄታ ያለው ምርታማ ግብርና ሥርዓት ግንባታ ላይ እንደአግባባቸው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅእኖ አላቸው::

አብዛኛዎቹ የልማት ባለሙያዎችና ምሁሮች እንደሚገልፁት የመሬት ይዞታ ሥሪት ለግብርናና ልማት ቁልፍ ሚና ይጫወታል:: የዘለቄታ የባለቤትነት ዋስትና የማይሰጥ የመሬት ሥሪት አርሶ አደሩ ንዋዩንም ሆነ ጉልበቱን ዘለቄታ ያለው ምርታማነትን በሚሰጡ የመሬት አጠቃቀቀም እና አያያዝ ቴክኖሎጂ ዎችና ተግባሮች ላይ እንዲያውል አይገፋፋውም:: የዚህም ዋና ምክንያት በንዋዩና በተግባሮቹ አማካኝነት የሚፈጠ ረው ጠቃሚ ውጤት ንዋዩን ያዋለው አርሶ አደር የሚያገኘው ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለሚሆን ነው::

በምሳሌ ለመግለጽ፣ ዘለቄታ ያለው ምርታማነትን ለመፍጠር የሚያገለግሉ እንደ ፍግ፣ ኮምፖስትና (የተዘጋጀ ብስባሽ ማዳበሪያ) የዛፍ ተክሎችና እህሎች ጣምራ ግብርና (Agro-forestry) የመሣሰሉ ቴክኖሎጂዎች መሬትን በረጅም ጊዜ ወስጥ ምርታማነቱን እንዲጨምር ይረዳሉ:: ሆኖም የመሬት ሥሪቱ የረጅም ጊዜ የባለቤትነትን ዋስትና ያረጋግጥልኛል ብሎ ካላመነ አርሶ አደሩ በነዚህ ቴክኖሎጅዎች ላይ ንዋዩን አያፈስም::

### *የጥናቱ ዓላማና ዘዴ*

የዚህ ፅሑፍ ዋነኛ ዓላማ የመሬት ሥሪት ከአርሶ አደሩ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ለውጥ ጋራ ያለውን ቁርኝት መመርመርና ጠቃሚ የፖሊሲ ሃሣቦችን መሰንዘር ነው:: ጽሑፉ የተመሠረተው

በ1992/1994 ዓ/ም በምሥራቅ ሸዋ እና በደቡብ ወሎ በተ ደረገ የናሙና ጥናት ላይ ነው:: ጥናቱ ካካተታቸው ጉዳዮች አንዱ ዘለቄታ ያለው ግብርና ለማጉልበት የሚያግዙ የመሬት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ሲሆን፣ ሌላው የመሬት መጠቀም መብት ሽግግር ሁኔታ ነው::

ጥናቱ በናሙናነት ከተመረጡ አርሶ አደር ቤተሰቦች በተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስቦአል:: ትንተናውንም አኃዛዊ (ስታስቲካዊ) ዘዴዎችን በመጠቀም አካሂዷል:: በተጨማሪም የቡድንና የነጠላ ውይይት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የግብርና ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ሽማግሌዎችና ወጣቶች ጋር በማካሄድ መረጃውን አጠናቅሮ ተጠቅሟል:: ከዚህም በላይ ሌሎች መፅሐፍትና ጽሁፎችን በመረጃና በፅንሰ ሀሳብ ምንጭነት ዋቢ አድርጓል::

## 2. ዋና ዋና የጥናቱ ግኝቶች

### *2.1 የአርሶ አደሩ የግብርና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አጠቃላይ ገጽታ*

እላይ እንደተጠቀሰው የአርሶ አደሩን ክፍለ ኢኮኖሚ በቀጣይነት ለማሳደግ ቴክኖሎጂያዊ መሻሻል (ለውጥ) አንዱ አስፈላጊ ሁኔታ ነው:: ይህም ማለት የአርሶ አደሩ እርሻ ቴክኖሎጂ መዋቅር ካለበት ዝቅተኛ ምርታማነትና አትራፊነት ደረጃ ወደ ከፍተኛ ምርታማነት፣ አትራፊነትና ዘለቄታዊነት ወደአለው ገበያ ተኮር ግብርና መሸጋገር ማለት ነው:: በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የአርሶ አደሩ የተሻሻለ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሁኔታ ሲገመገም በጣም ዝቅተኛ ነው:: ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ መስፋፋት በመደበኛ አሠራር ከተጀመረበት 1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያሳየው ቴክኖሎጂያዊ የለውጥ ሂደት እጅግ አዝጋሚ ነው:: ይህም የአገሪቱ የግብርና ቴክኖሎጂ ልማትና ስርጸት ሥርዓትን መልሶ ማጤን እንደሚያስፈልግ ያመላክታል::

የሚከተሉት አሐዛዊ መረጃዎች እላይ የተጠቀሰውን እንድምታ ያጠናክራል:: በአገር ደረጃ በሥርጭት ላይ የሚገኙት ዋነኞቹ ቴክኖሎጂዎች የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎችና የኬሚካል የአፈር ማዳበሪያ ናቸው:: ይሁን እንጂ በተሻሻሉ ዝርያዎች የሚዘራው የብርዕ፣ የአገዳና የጥራጥሬ መሬት ከጠቅላላው በነዚሁ ሰብሎች ከሚሸፍነው መሬት ወስጥ አምስት ከመቶ ያህል ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ ከብርዕና አገዳ ሰብሎች ጠቅላላ መሬት ወስጥ ማዳበሪያ የሚያገኘው መሬት አርባ አራት ከመቶ የሚሆነው ነው:: የተሻሻሉ እርሻ መሣሪያዎች ልማትና ሥርፀት ከቁጥር የሚገባ አይደለም:: እንዲሁም የሰብል ተባይና በሽታ መከላከያ መድሃኒት አጠቃቀም አናሳ ነው::

በደቡብ ወሎ በተመረጡ ናሙና ቀበሌዎች በተደረገው ጥናት በጥቅሉ የማዳበሪያ ተጠቃሚ አርሶአደር ቁጥር ሃያ አምስት በመቶ ብቻ ሲሆን፣ አንድ ቤተሰብ በአማካይ ከ25 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ማዳበሪያ ይጠቀማል (ሠንጠረዥ አንድ ላይ ይመልከቱ):: የተሻሻሉ ዝርያ አጠቃቀም በሚመለከት በዚሁ ሠንጠረዥ እንደሚታየው በነፍስ ወከፍ ቤተሰብ ደረጃ ከአራት ኪሎ ግራም ያነሰ ሲሆን፣ የተጠቃሚውም ብዛት ከመቶ 12 ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ የአጠቃቀም ሁኔታ ከወረዳ ወረዳ ይለያያል:: ለምሳሌ ጃማ ወረዳ በአየር ንብረቱና በመልክዓ ምድሩ በአንፃራዊ ሁኔታ ለግብርና የሚስማማ በመሆኑ የማዳበሪያና የተሻሻለ ዝርያ አጠቃቀሙ በአማካይ በመጠንም ሆነ በተጠቃሚ የቤተሰብ ብዛት በጣም የተ ሻለ ነው:: በአንፃሩ ባቲ ወረዳ ዝናብ አጠር አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያያዞ በማዳበሪያም ሆነ በምርጥ ዘር አጠቃቀሙ ከግምት የሚገባ አይደለም::

*<u>ሠንጠረዥ 1</u>: በደቡብ ወሎ የማዳበሪያና ምርጥ ዘር አጠቃቀም ሁኔታ (1994 ዓ/ም)*

| ዓይነት | ወረዳ | የቤተ ሰብ ናሙና ብዛት | መጠን | የተጠቃሚው ብዛት(%) |
|---|---|---|---|---|
| ማዳበሪያ በኪ/ግራም | ባቲ | 110 | 0.51 | 2.73 |
| | ጃማ | 104 | 87.6 | 70.19 |
| | ደሴ ዙሪያ | 100 | 8.83 | 24.00 |
| | ሊጋምቦ | 106 | 2.90 | 5.68 |
| ጠቅላላ | | 420 | 24.66 | 25.24 |
| የተሻሻለ የእህል ዝርያ በኪ/ግራም | ባቲ | 110 | 0.71 | 5.45 |
| | ጃማ | 104 | 8.97 | 23.08 |
| | ደሴ ዙሪያ | 100 | 3.32 | 15.00 |
| | ሊጋምቦ | 106 | 1.58 | 6.60 |
| ጠቅላላ | | 420 | 3.60 | 12.38 |

### *2.2 የመሬት ሥሪትና የአርሻ መሬት መብት ሽግግር (ግብይት)*

በ1997ቱ ሕገ መንግሥት እንደተደነገገው በኢትዮጵያ መሬት የመንግሥት ነው:: አርሶ አደሩ በመሬት የመጠቀም መብቱን ወደ ሌላ የማሸጋገር መብት አለው:: ስለዚህም የመሬት ሥሪት የሚመነጨው መንግስት በሚያደርገው የመሬት ድልድል ወይም አርሶ አደሩ የእርሻ መሬቱን የመጠቀም መብት ለሌላ ተጠቃሚ ሲያሸጋገር ነው:: በይበልጥ የሚታወቁት የመሬት መብት መሸጋገሪያ መንገዶች ኪራይ፣መጋዞ (የእኩል/ሲሶ) እና ስጦታ ናቸው::

ይህ ፅሑፍ መሠረት ያደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው የመሬት መጠቀም መብት ማሸጋገር በተለይ በኪራይና መጋዞ አማካኝነት የሚፈፀመው የመሬት መብት ግብይት ቡዙውን ጊዜ በግልጽና በአደባባይ አይደለም:: ሽግግሩ የሚፈፀመው በመተዋወቅና በሚተማመኑ ተገባያዬች መሀከል ባህላዊ በሆነ መንገድ ነው:: አርሶ አደሮቹ እንደሚገልፁት እነሱ በሚፈልጉት ደረጃ ግልጽና ተአማኒ የሆነ የመሬት መብት ደንቦችና ሥርዓቶች የሉም:: ከሁለም በላይ የሚካሄዱትን የመሬት መብት ግብይቶችንና ስምምነቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ የማስፈፀም አቅም ያላቸውና የሚተማመኑባቸው የመንግስት አካሎች (ቀበሌዎች) በአቅራቢያቸው ያለመኖራቸው ችግሩን አባብሷል:: ግብይቱንም የሚፈፅሙት ፈራ ተባ ባለ ሁኔታና ከግብይቱ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሁሉ ባረጋገጠ መልክ አይደለም:: ከዚህም በላይ መሬት በኪራይም ሆነ በመጋዞ ለሌላ

ተጠቃሚ የሚሸጋገረው ለጥቂት አመታት ብቻ ነው (ለምሳሌ 2-3 ዓመታት):: በምሥራቅ ሸዋ የአዳሚቱሉ ጃዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ናሙና አርሶ አደሮች እንደጠቆሙት መሬታቸውን ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚያከራዩት ወይም በመጋዞ የሚሰጡበት ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው::

1ኛ. በኪራይ ወይም በመጋዞ ከሰጡ በኋላ የሚመጡት የመኸር ወቅቶች አመቺና ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል መሬቱን እራሳቸው ለመጠቀም በመፈለግ፣

2ኛ. በኪራይ ወይም በመጋዞ ከሰጡ በኋላ በሚመጡት የመኸር ወቅቶች እራሳቸው ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር የመግዛት አቅም ኖሯቸው መሬቱን ማረስ በመፈለግ፣

3ኛ. ምንአልባት መሬቱን የተከራየው ወይም በመጋዞ የወሰደው ተጠቃሚ በተንኮል ከመሬቱ ጋር በተያያዘ

ችግር ወይንም ክስ ቢፈጥር አተካራ ውስጥ ላለመግባት::

4ኛ. ምንአልባት መንግስት መሬት የማደላደል የፖሊሲ እርምጃ በመሀሉ ቢወስድ ክርክርና አታካራ ውስጥ እንዳይገቡ በመስጋት ነው::

እነዚህ *ሥጋቶችና* ጥርጣሬዎች መሬትን ከፍተኛ ጥቅምን በሚያስገኝና ቀልጣፋ በሆነ መልክ ጥቅም ላይ እንዳይውል እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ:: በተጨማሪም ስጋቶቹ መሬት የመጠቀም መብት ግብይትን ቀልጣፋና ውጤታማ እንዳይሆን መሰናክል ይሆናሉ::

ጥናቱ እንዳመለከተው በዚሁ ወረዳ በወቅቱ መሬትን በመጋዞ በመስጠትም ሆነ በመቀበል የተሳተፉት ሃያ አራት ከመቶ ሲሆኑ መሬትን በኪራይ በመስጠትም ሆነ በመውሰድ የተሳተፉት ደግሞ ሃያ ስድስት ነጥብ አምስት ከመቶ ናቸው:: ይህም የመሬት መጠቀም መብት ግብይት መጠን ውስን እንደሆነ ያመለክታል:: ከዚህ በተ ጨማሪ መሬትን በኪራይም ሆነ በመጋዞ ለሌላ ተጠቃሚ የሚያሸጋግሩት በአብዛኛው ጊዜ እማወራ ቤተሰብና ባጠቃላይ የጉልበት፣ የበሬ፣ እና የገንዘብ ዕጥረት ያለባቸው ቤተሰቦች ናቸው::

## 2.3 የመሬት *ሥሪትና* የግብርና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ዘለቄታ ያለው ምርታማ የአርሶ አደሩን ክፍል ኢኮኖሚ ለማጐልበት አፈር ጥበቃና የአፈርን ለምነት ማዳበር ወሳኝ ነው:: በተለይም በእርሻ ማሳዎች ላይ የሚደርሰውን የአፈር መከላት መግታት አስፈላጊ ነው:: የኢትዮጵያ ከፍተ ኛ ቦታዎች ለዚህ አደጋ የተጋለጡ ናቸው:: በዓመት ከአንድ ሄክታር ላይ እስከ 42 ቶን የሚደርስ ለም አፈር ተጠርጎ ይሄዳል:: ይህንንም ችግር ለመቀነስና ለመግታት የተሻሻሉ ዘለቄታ ያለው የመሬት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችና ተግባሮች ማከናወን አስፈላጊ ነው:: ሰብል ማፈራረቅ፣ ፍግና ብስባሽ ለአፈር ማዳበሪያነት መጠቀም፣ የአፈር መከላትን የሚከላከሉ የአስተራ ረስ ዘዴዎችና፣ የማሳ ላይ ክትሮች፣ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ጥቂት የቴክኖሎጂዎችና የመሬት አያያዝ ዘዴ ዎች ናቸው::

እላይ በተራ ቁጥር 2.2 እንደተመለከተው ዋስትና የሌለው የመሬት ይዞታ *ሥሪትና* የመሬት መብት ግብይት ዘለቄታ ያላቸው ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ:: ይህን በተመለከተ ጥናቱ እንደሚያመለክተው በኪራይም ሆነ በመጋዞ የተያዙ ማሳዎች ላይ የሚደረገው የኬሚካል ማዳበሪያም ሆነ የዘለቄታ ምርታማነትን የሚያግዘው ፍግና ብስባሽ በራስ ይዞታ በሆኑት ማሳዎች ላይ ከሚደረገው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው:: ለምሳሌ በምስራቅ ሸዋ አዳሚቱ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ጥናት፣ አሥራ ዘጠኝ ከመቶ የሚሆኑት የራስ ይዞታ ማሳዎች ዳፕ ማዳበሪያ ሲደረግላቸው በኪራይ /መጋዞ ከተያዙት መቶ ማሳዎች አስራ አምስት ፐርሰንት ብቻ ናቸው ዳፕ የተደረገላቸው::

በተጨማሪም በራስ ይዞታ ስር በሚገኙ ማሳዎች ላይ የተደረገው የማዳበሪያ መጠን 28.4 ኪ/ግራም በጥማድ ሲሆን፣ ይህም በኪራይ /መጋዞ ከተያዘው ማሳ ላይ ከሚደረገው መጠን አስራ ዘጠኝ ነጥብ አራት ኪ/ግራም በጥማድ የላቀ ነው::

በተመሳሳይ ሁኔታ ሃያ አምስት ነጥብ አምስት ከመቶ የሚሆኑት በራስ ይዞታ *ሥር* የሚገኙት ማሳዎች ፍግ ሲደረግላቸው 10.6 ከመቶ የሚሆኑት በኪራይ/መጋዞ የተ ያዙ ማሳዎች ብቻ ፍግ ተደርጎላቸዋል::

ብዛታቸው አነስተኛ ቢሆንም ሰብል ማሰባጠር፣ መስኖ ውሃ፣ እና እህል ዛፍ ስብጥር ግብርና አሠራሮች የተከናወኑት በራስ ይዞታ *ሥር* በሚገኙ ማሳዎች ብቻ ነበር::

በጥቅሉ አርሶ አደሩ ዘለቄታነት ያለው የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን የሚተገብረው የራስ ይዞታ በሆነት ማሳዎች ላይ እንጂ በኪራይ ወይም በመጋዞ በተያዙት ማሳዎች ላይ አይደለም:: ይህም የሆነበት ዋነኛው ምክንያት መሬት በኪራይም ሆነ በመጋዞ የሚሰጠው ለአጭር ጊዜ በመሆኑና የመሬት *ሥሪቱ* ለመሬት መብት ግብይት ዘለቄታ ዋስትና ካለመስጠቱ ጋር የተያያዘ ነው:: ይህም አርሶ አደሩ በረጅም ጊዜ ውስጥ ጥቅም የሚሰጡትን ቴክኖሎጂዎች የሚጠቀመው በአንፃራዊ ደረጃ የተሻለ የይዞታ ዋስትና ባላቸው ማሳዎች ላይ መሆኑን ይጠቁማል::

## *2.4 የመሬት ይዞታ መጠንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም*

በመግቢያ እንደተጠቀሰው በነፍስ ወከፍ ይዞታ ስር ሆኖ አርሶ አደሩ የሚጠቀምበት የግል እርሻ መሬት ስፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መጥቷል:: እያደገ የሚሄደው የሕዝብ ብዛት አማራጭ የኑሮ መተዳደሪያ ምንጮች ማነስ ጋር ተጣምሮ የይዞታ መጠንን መሽቆልቆል አባብሶታል::

የተለያዩ ጥናቶችም እንደሚጠቁሙት ቴክኖሎጂን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና የእርሻ ምርታማነትን ለመጨመር በቂ የእርሻ መሬት አስፈላጊ ነው:: በዚህ ረገድ ቀልጣፋና ውጤታማ አፈፃፀም ያለው የመሬት መብት ግብይትና ዋስትና ያለው የተረጋጋ የመሬት *ሥሪት* ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: ይህ ዓይነቱ የመሬት *ሥሪት* በነፍስ ወከፍ ደረጃ የሚታረሰውን የመሬት ስፋት የማጐልበትና ምርታማነትን የማስፋፋት ዕድል ይከፍታል:: የእርሻ መሬት በሰፋ ቁጥር በጥማድ ወይም በሄክታር ደረጃ ያለው የማዳበሪያም ሆነ የሌሎች ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ወጪ እየቀነሰ ይሄዳል::

በደቡብ ወሎ የተካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው የመሬት ይዞታ መጠን በሰፋ ቁጥር አርሶ አደሩ የላቀ የማዳበሪያ መጠን ይጠቀማል:: በሌላ በኩል አነስተኛ የመሬት መጠን ያላቸው አርሶ አደሮች በኤክስቴንሽንና በብድር አገልግሎት ተጠቃሚነታቸው ከፍ ያለ የመሬት መጠን ካላቸው አርሶ አደሮች ጋር ሲነፃፀር አናሳ ነው:: ይህም ባለ አነስተኛ የመሬት ይዞታ አርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ለውጥ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል::

በዚሁ ጥናት የቤተሰብ የመሬት መጠን በሦስት ቡድን ማለትም በአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ቡድን ተከፍለው የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን ለማወዳደር ተሞክሯል:: በዚሁ መሠረት ከአነስተኛ ወደ መሀከለኛ ከዚያም ወደ ከፍተኛ የእርሻ ይዞታ መጠን በተሸጋገሩ ቁጥር የኬሚካል ማዳበሪያ፣ የተሻሻሉ ዝርያ ዎችና የፍግ መጠን በጎላ ሁኔታ እየጨመረ ይሄዳል (ሠንጠረዥ ሁለት ይመልከቱ):: ይህም ልዩነት የመነጨው በአጋጣሚ ሳይሆን ከመሬት መጠን ልዩነት የተነሣ መሆኑ በስታስቲካዊ ትንተናና ምዘና ተረጋግጧል::

ሠንጠረዥ 2. *በደቡብ ወሎ የተሻሻለ ዝርያ፣ የኬሚካል ማዳበሪያና የፍግ አጠቃቀም በመሬት ይዞታ መጠን አንፃር ሲታይ*

| ዓይነት | አነስተኛ (≤0.5 ሄክታር) | መካከለኛ (0.51-2.00 ሄክታር) | ከፍተኛ (>2.0 ሄክታር) |
|---|---|---|---|
| የኬሚካል ማዳበሪያ ኪ/ግ | **1.40** | **23.69** | **27.83** |
| የተሻሻሉ ዝርያዎዎች ኪ/ግ | **-** | **0.42** | **2.67** |
| ፍግ ኪ/ግ | **16.97** | **74.66** | **140.92** |

ይህ ውጤት የእርሻ መሬት ይዞታ ከፍ ማድረግ አርሶ አደሮች ምርታማነትን የሚጨምሩ የተሻሻሉ ግብአቶችንንና ለዘለቄታ የሚጠቅሙ ቴክኖሎጂ ዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ያመለክታል፡፡

## 3. ለፖሊሲ ጠቀሜታ ያላቸው የመደምደሚያ ነጥቦች

ከጥናቱ ግኝቶች የመነጩት የፖሊሲ ሃሣቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የኬሚካል ማዳበሪያና ሌሎች ዘለቄታ ያለውና የመሬትን ምርታማነት የሚጨምሩ ቴክኖሎጂዎችና ሥራዎችን ማከናወን ለአርሶ አደሩ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ አርሶ አደሩ የበሬና የብድር አገልግሎት የሚያገኝበትን መንገድ መቀየስ ያሻል፡፡

የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤታማነት ከአካባቢው ሥነ-ምህዳር ሁኔታ ጋር የሚያያዝ መሆኑ በትንታኔ ውስጥ ታይቷል፡፡ ስለዚህም አንፃራዊ በሆነ መልኩ ለግብርና ምቹነት ለሌለው አካባቢ ከግብርና ውጪ የሆኑ ሥራ ዎችን ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም የተለያዩ ሥነ-ምህዳሮችን ያገናዘበ የግብርና ዕቅድ ሥራ ጠቀሜ ነው፡፡ እቅዱም የተለያዩ ቦታዎችና ሥነ-ምህዳሮችን በተነፃፃሪነት በበለጠ በሚጠቅሙበት ቦታ ታጭተው እንዲጎለብቱ ይ ረዳል፡፡

የአርሶ አደሩ የመሬት ይዞታ መጠን በጨመረ ቁጥር አርሶአደሩ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነቱ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ የተበጣጠሱ ማሳዎችን አንድ ላይ ማጐልበት የእርሻን ሥራ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ምርታማ ለማድ ረግ ያግዛል፡፡

በሌላ በኩል አርሶ አደሩ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት እንዳይጠቀም የሚያግዱትን ከመሬት ሥሪት ጋር የተያያዙም ይሁኑ ያልተያያዙ ነገሮችን በተለያዩ ቦታ ዎችና ሥነ-ምህዳሮች በዝርዝር ማጥናት ይገባል፡፡

ፈጣን ቴክኖሎጂያዊ ለውጥ በአርሶአደሩ ክፍለኢኮኖሚ ለማምጣት የግብርና ምርምርና ስርፀት ተቋሞች የአካባቢ ሥነ-ምህዳርን፣ ባህላዊ ቴክኖሎጂዎችንና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ስትራቴጂዎችንና መንገዶችን መልሶ ማጤንና መተለም ይገባቸዋል፡፡

የእርሻ መሬት መብት ሽግግር (ግብይት) የእርሻ መሬትን ስፋት ለመጨመርና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ይረዳል፡፡ ስለዚህ የመሬት መብት ሽግግር ለረጅም ጊዜ ያለሥጋት እንዲከናወን የበለጠ ዋስትና የሚሰጥ ሐጋዊና ተቋማዊ አሠራር ላይ ተመስርቶ የሚፈፀም የመሬት ስሪት ፖለሲን ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡

ምርት የሚጨምሩ የተሻሻሉ ግብአቶችና ዘለቄታ ያለው ግብርናን የሚያጐለብቱ ቴክኖሎጂዎች አርሶ አደሩ በኪራይ /መጋዞ/ ከያዛቸው ማሣዎች ይልቅ በራሱ ይዞታ ሥር ባሉት ማሳዎች ላይ ማድረግን ይመርጣል፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያቱ የመሬት ሥሪቱ ለረጅም ጊዜ የመሬት መብት ሽግግር በአስተማማኝ መልክ እንዲካሄድ ዋስትና ስለማይሰጥ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአገሪቱ የተጀመ ረው የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ሰርተፊኬት ለአርሶ አደሩ መስጠት ለመሬት ይዞታና ለመሬት መብት ግብይት የተሻለ ዋስትና ይሰጣል ተብሎ ቢገመትም ለዘለቄታው ዋስትና ለመስጠት የመሬት ሥሪቱን የዋስትናን ፅንሰ ሃሣብ መሠረት አድርጐ ማጤንና ማሻሻል ጠቃሚ ነው፡፡ በተጨማሪም የመሬት ባለቤትነት ሰርተፊኬት ለብድር አገልግሎት ሰጪዎች በዋስትናነት እንዲያገለግል እንዴትስ እንደሚፈፀም ማጥራት አስፈላጊ ነው፡፡ የመሬት ባለቤትነት ሰርተፊኬት ሂደትና ሰርተ ፊኬቱ በግብርናው ልማትና ቴክኖሎጂ ለውጥ ላይ ያለውን ሚና በቀጣይነት በስፋት ማጥናት ይገባል፡፡

እላይ በተጠቀሰው መልክ የሚደረግ የሥሪት መሻሻል ቀልጣፋ አመራረትን፣ ቴክኖሎጂያዊ ለውጥን፣ ዘለቄታ ያለው የመሬት አያያዝና አጠቃቀምን ብሎም የምግብ ዋስትናን ለማጐልበት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

የመሬት ሥሪት መሻሻል ሰፊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችንና ችግሮችን ሊያስቀሩ በሚችሉና በሕግ ፊት እኩለነትንና ዘላቂነትን በሚያረጋግጡ የፖሊሲ እርምጃ ዎች ሊታገዝ ይገባል፡፡ ለዚህም የማስፈፀም አቅሙ የጐለበተ የመሬት ይዞታንና የመሬት መብት ሽግግርን ሕግን ተንተርሶ የሚያስተዳድርና የሚተገብር ተቋም አስፈላጊ ነው፡፡

በተጨማሪም በመሬት ሥሪትና ቴክኖሎጂያዊ ለውጥ ጉዳይ ላይ ሁሉንም ያሳተፈ ጥናትና ልምድ ላይ የተመሠ ረተ ወይይቶችን የሚያካሂዱ ተቋሞችና መድረኮችን ማገዝና አዲሶችም እንዲፈጠሩ ማበረታታት ጠቃሚ ነው፡፡

ይህ ውጤት የእርሻ መሬት ይዞታ ከፍ ማድረግ አርሶ አደሮች ምርታማነትን የሚጨምሩ የተሻሻሉ ግብአቶችንንና ለዘለቄታ የሚጠቅሙ ቴክኖሎጂ ዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ያመለክታል፡፡

**(ወርቅነህ ንጋቱ፣ዶ/ር)**

*ምንጭ:-* Workneh Negau. 2006. "Land tenure and technological improvement in smallholder agriculture in Ethiopia." In *Land and the challenge of development in Ethiopia*, edited by Dessalegn Rahmato and Taye Assefa, p.147-165. Addis Ababa: Forum for Social Studies.

**Acknowledgement & Disclaimer**

*This document has been produced with the financial assistance of the European Union. The contents of this document are the sole responsibility of the author and can under no circumstances be regarded as reflecting the position of the European Union.*

አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79
ኢ.ሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et